የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia Office of the Federal Auditor General

ቁጥር Ref.No ፌዋኦ 9.2/350
ቀን Date 23/09/2011

ለተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ
የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት አፈጉባዔ
<u>አዲስ አበባ</u>

ጉዳዩ፡- <u>ማስተካከያ ስለመላክ</u>

የመ/ቤታችን የተጠቃለለ ዓመታዊ ኦዲት ሪፖርት በቁጥር ፌዋኦ 9.2/336 ግንቦት 7/9/2011 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ መላኩና ግንቦት 22/2011 ዓ.ም የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት ለፓርላማ መቅረቡ ይታወሳል፡፡

በዚሁ የተጠቃለለ አጭር ሪፖርት ላይ ከተመለከቱት ነጥቦች፡-

1. ገጽ 18 ፓራግራፍ 65 ማስረጃ ሳይኖር በወጪ የተመዘገበና ትክክለኛነቱን ማረጋገጥ ያልተቻለ ሂሣብ ከተገኘባቸው መ/ቤቶች ዝርዝር ውስጥ የውጭ ጉዳይ ሚ/ር ብር 129,001,549.44 የተባለው ዘግይቶ ማስረጃ በመቅረቡ ወደ ብር 50,633,757.50 የተስተካከለ ስለሆነ መጀመሪያ የተጠቀሰው ከዕርማቱ በፊት በመሆኑ ሁለተኛው ትክክለኛ እንደሆነ ተደርጎ እንዲወሰድልን፣
2. ገጽ 47 ፓራግራፍ 167 የተጠናቀቁ ልዩ ኦዲት ዝርዝር አባሪ ያልተያያዘ በመሆኑ 1 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ያያያዝን መሆኑ፣ (ይኸው ዝርዝር በአጠቃላይ ዘገባ ጥራዝ 2 ከገጽ 222 - 223 የተመለከተ ስለሆነ በሪፖርቱ ገጽ 54 ፓራግራፍ 190 ስር እየተሠሩ ያሉት ልዩ ኦዲቶች 14 ሳይሆኑ 11 ብቻ ናቸው፡፡)
3. ገጽ 56 ፓራግራፍ 196 የተመለከተው ሀሳብ በስህተት የተደገመ ስለሆነ ሁለቱም መስመር መሰረዝ ያለበት መሆኑ፣

ገመቹ ዱቢሶ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር

4. በገጽ 60 የተያያዘው አባሪ ውስጥ የኦዲት አስተያየትን በተመለከተ፡- 4ኛ አምድ (column) የ2010፣ 5ኛ አምድ (column) የ2009፣ 6ኛ አምድ (column) እና የ2008 በጀት ዓመት ሂሣብ የሚያሳይ መሆኑን እና በሠንጠረዡ ዝርዝር የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ስር ተራ ቁጥር 11 የኢትዮጵያ ብዝኃ ህይወት ኢንስቲትዩት የ2010 በጀት ዓመት አስተያየት መስጠት ያልተቻለ የ2009 እና የ2008 ደግሞ የጎላ ችግር ያለበት በመሆኑ ተቀባይነት የሚያሳጣ አስተያየት የተሰጠበት መሆኑን፣ እየገለጽን ለተፈጠረው ስህተት ከልብ ይቅርታ እንጠይቃለን፡፡

ከማክበር ሰላምታ ጋር

ገመቹ ዱቢሶ
ፌዴራል ዋና ኦዲተር

<u>ግልባጭ፣</u>

በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት
ለመንግስት ወጪ አስተዳደርና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ
<u>አዲስ አበባ</u>

# ልዩ ኦዲት የተካሄደባቸው መ/ቤቶችና የኦዲት አርዕስቶች

| ተ.ቁ | የመ/ቤት ስም | የልዩ ኦዲቱ አርዕስት/ ጉዳይ |
|---|---|---|
| 1 | የኢንፎርሜሽን መረብ ደኅንነት ኤጄንሲ - | የሳይበር ታለንት ማነጅሜንት ፕሮግራም |
| 2 | አዲስ ቪው ጄንራል ሰርቪስ ኃ/የተ.የግል ማህበር- | 2001-2009 ዓመታት ከግብር አከፋፈል ጋር የተያያዘ |
| 3 | በገንዘብ ሚኒስቴር- | የተቀናጀ የፋይናንስ አስተዳደር ስርዓት ዝርጋታ ፕሮጀክት፤ |
| 4 | የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት- | አለም አቀፍ የስንዴ ግዥን የጨረታ ሂደት በተመለከተ |
| 5 | | የታብሌት ግዥን በተመለከተ |
| 6 | | የ HP Computer ግዥን በተመለከተ |
| 7 | የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን- | የህዳሴ ግድብ የደን ምንጣሮ የአገልግሎት ግዥ በተመለከተ |
| 8 | | የ114 የመኪና ግዥን የግዥ ሂደት በተመለከተ |
| 9 | የጂኦሴንቴቲክስ ኢንዱስትሪያል ወርክስ ኃ.የተ.የግል ማህበር- | ከጎልደን ትሬዲንግ ጋር የተደረጉ ግዥዎች ፤ የግዥ ደንብና መመሪያን ተከትለው ስለመፈጸማቸው፤ |
| 10 | የወንዶ ገነት ግብርና ምርምር ማዕከል | ሀዋሳ በቆሎ ምርምር መለስተኛ ማዕከል የግንባታና ቢሮ ዕድሳት፣ |
| 11 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ አገልግሎት፣ | የባቱ ዲስትሪክት አገልግሎት መስጫ ማዕከል የአንድ ገንዘብ ያዥ ሂሳብ |
| 12 | አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ- | ከፅዳት አገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ |
| 13 | አንበሳ ባንክ፡- በፍ/ቤት ትህዛዝ- | የአዳማ ልዩ ዞን ከ/ፍርድ ቤት ጠያቂነት በአንበሳ ባንክና በአንድ ገንዘብ ያዥ የጥሬ ገንዘብን ጉድለትን በተመለከተ |
| 14 | ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር-- | በጅዳ ሳዑዲ አረቢያ በሚገኘው የኢትዮጵያ ቆንስላ ፅ/ቤትና በኢትዮጵያዊያን ኮሚኒቲ ማህበራት መካከል ከገንዘብ አስተዳደርና አያያዝ ጋር በተመለከተ |